# በዜጎች የሚነግዱትን መግታት!!

ይነበብ ይግለጡ 05-16-17

በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የተነሳ የብዙ ሺህ ዜጎች ሕይወት አደጋ ላይ ወድቆ ቆይቷል፡፡ በሕግ በኩል የሚወሰደው እርምጃ እንዳለ ሆኖ ለማስቆም የሚችለው ትልቁ ኃይል ከመንግስት በተጨማሪ ዋናው ሕዝብ ነው፡፡ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የኑሮአቸውና የመክበሪያቸው መሰረት የሆነው በሕገወጥ መንገድ ዜጎችን እየደለሉና እያታለሉ ወደተለያየ ሀገራት እንወስዳችኃለን የተሻለ ሕይወት ትኖራላችሁ በሚል የሚፈጽሙት ወንጀል ነው፡፡በዜጎች የሚነግዱትን ግለሰቦችና ቡድኖች መግታት ግዴታ ነው፡፡

ወደ ውጭ ሀገራት ለመሄድ ይሄን ያህል ገንዘብ በጥሬው መክፈል አለባችሁ በሚል ከሕብረተሰቡ በገፍ ብር እየሰበሰቡ በርካታ ዜጎችን ከሀገራቸውና ከሰላማዊ ኑሮአቸው አስኮብልለዋል፡፡ የተገባላቸው ቃል ሳይፈጸምላቸው ቀርቶ በእነሱ መደለያ ተታለው ሕይወታቸውን ላጡት በመንገድ የት እንደደረሱ ሳይታወቁ አድራሻቸው ሳይገኝ በባሕር ሰምጠው ለቀሩት አውሬ በየዱሩ ለበላቸው ሁሉ ተጠያቂዎቹ ፤ የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤዎች በሕገወጥ አዘዋዋሪነት የተሰማሩ ሰዎች ናቸው፡፡

ህገወጥ የሰው ደላሎች ማለት  በሰው ሕይወት የሚነግዱ ለከፋ አደጋ አጋልጠው የሚሰጡ ገና ለገና ገንዘብ እናገኛለን ብለው የዜጎቻቸውን ሕይወት ያልተጠበቀ ችግርና አደጋ ውስጥ የሚጥሉ ገንዘብ  እስካገኙ ድረስ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ እንደ ባሪያ ንግድ ዘመን የሚሸጡና የሚለውጡ ናቸው፡፡ይሄን አስነዋሪ ድርጊት ለመከላከል መንግስት በራሱ በኩል በከፍተኛ መንግስታዊ አመራር ደረጃ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ እየሰራ ቢሆንም ከችግሩ ስር መሰደድ የተነሳ በአጭር ጊዜ መፍትሔ ለማስገኘት አይሞከርም፡፡

በሚዲያ አማካኝነት ለረዥም ጊዜ ሰፊ ስራ መሰራት አለበት፡፡በሁሉም የሀገሪቱ ቋንቋዎች በመጠቀም ለሁሉም የሀገሪቱ አካባቢ ሕዝብ ተደራሽ የሚሆን ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን አስከፊ ስራና በእነሱ መነሻነት የሚከሰተውን ስደት ጥፋትና ሞት የሚያስከትለውን የዜግነት ክብርን የሚነካ አስከፊ አደጋ የተመለከተ ስራዎችን በመስራት

የአመለካካት ለውጥ ማምጣት እስካልቻልን ድረስ ችግሩ ይቀጥላል፡፡የሚጠበቀውን ለውጥ ለማምጣት ረዥም ርቀት ሄደን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

ሕገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎችን አስከፊ ስራና ይህን ተከትሎ የሚመጣውን የዜጎች ስደት በየቀኑ ማስተማርና ግንዛቤ ማስጨበጥ ህብረተሰብ ትምህርት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ የኢኮኖሚ ስደት ሕይወትን የተሻለ አድርጎ ለመለወጥ ከመጓጓት ጋር ተያይዞ የሚከሰት ነው፡፡ በአረብ ሀገራት ባልታወቁ እስርቤቶች ውስጥ ታስረው የሚማቅቁ ኢትዮጵያውያን ዜጎች መኖራቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

መንግስት በሕገወጥ መንገድ የወጡትን በተመለከተ መረጃው ሲደርሰው ብቻ ነው ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን አውቆ ዜጎቹን ለማዳንና ወደሀገራቸው ለመመለስ በትኩረት የሚሰራው፡፡ ይህ በመሆኑም ሕይወትህ(ሽ) ይለወጣል ፤ብዙ ገንዘብ ታገኛለህ ታገኚያለሽ እየተባሉ ያለምንም ሕጋዊ ዋስትናና ጥበቃ ሕይወታቸውን ለአደጋ ሰጥተው በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡት ዜጎች የከፋ አደጋ ላይ ወድቀው ይገኛሉ፡፡

ዛሬም በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች በሕገወጥ መንገድ የሰው ሀገር ድንበር ጥሰው የገቡና የተያዙ ፍርድቤት ቀርበው የተፈረደባቸው ፍርድ ሳያገኙም እየተጠባበቁ የሚገኙ ዜጎቻችን ብዙ ናቸው፡፡እነዚህ ዜጎች ከመውጣታቸው በፊት በሕጋዊ መንገድ ሄደው ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ፈተናና መከራ አይገጥማቸውም ነበር፡፡መንግስት በዜጎቹ ጉዳይ በሚፈጠረ ማንኛውም ሁኔታ በመነጋገር ችግሩን ይፈታዋል፡፡አሁንም ቢሆን ጉዳዩን በዝምታ አይመለከተውም፡፡

በአሁኑ ወቅት የስደትንና የስራ አጥነትን ችግር ለመቅረፍ ሀገራችን ሰፊ የስራ መስኮችን እየፈጠረች ያለች በመሆንዋ ዜጎች አላስፈላጊ መስዋዕትነት በመክፈል ሕይወታቸውን ሊያጡ አይገባም፡፡ ነገ የተሻለ ቀን ነው ፤ነገ በሀገሬ ላይ ሰርቼ የማደግ የመለወጥ የማግኘት ሰፊ እድል አለኝ ብሎ የሚያስብ በራሱ ሀገር የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር ሰፊ ስራ መሰራት አለበት፡፡

በተለያዩ የአረብ ሀገራት ከመቶሺዎች በላይ የሚገመቱ ዜጎቻችን በሕገወጥ መንገድ ገብተው እንደሚኖሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡የሚደርስባቸውን በደልና ግፍ አውቆ ለመከላከል የሚያስችሉ ቀጥተኛ ግንኙነት ከመንግስት ጋር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ለመከራከርም ሆነ ለመነጋገርም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ጉዳዩን ያወሳስበዋል፡፡

ከዚህ ሁሉ የተሻለው አማራጭ ዜጎች ውጭ ወጥተው መስራት ከፈለጉ መንግስት አውቆት በሕጋዊ መንገድ ቢሄዱ አስተማማኝ ሕጋዊ ዋስትና ያገኛሉ፡፡ ዜጎቹም በተመለከተ በሚፈጠረው ማንኛውም ጉዳይ መንግስት በቀጥታ ጣልቃ መግባትና መነጋገር ይችላል፡፡ እስከዛሬ ከሀገራችን ስንት ዜጎች በሕገወጥ መንገድ ወጡ? ምንስ ደረሳባቸው ? የሚለው ጉዳይ ሰፊ ጥናትና ክትትልን ይጠይቃል፡፡ ትምህርት ሰጪነቱ ለትውልድ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡የዚህ ጉዳይ ዋነኛ ባለቤቶች በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ይሄንኑ ነውረኛ ተግባር መተዳደሪያቸውና መክበሪያቸው ያደረጉ ሰዎች በመላው ሀገሪቱ ተንሰራፍተው መረባቸውን ዘርግተው መገኘታቸው ነው፡፡

እነዚህ ህገወጦች በሕግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ቢኖሩም ዋነኛና አንቀሳቃሽ የሚባሉትን በተመለከተ በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ስራ መሰራት አለበት፡፡ ለችግሩ ቁልፍ መፍትሔ የሚሆነው ስደትን የሚጠላና የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር ነው፡፡ይህም ሰፊ ጊዜንና ጠንካራ የሚዲያ ስራን ይጠይቃል፡፡አጋጣሚ ሲፈጠር ብቻ የሚሰራ የሚዲያ ስራ ውጤታማ አይደለም፡፡ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ነው፡፡የሚዲያ ስራ ተሰራ የሚባለው በሕዝቡ ልቦናና መንፈስ ውስጥ ነግሶ የሚኖር ስራ ሲሰራ ብቻ ነው፡፡

ሀገራችን ድህነትን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል ሰፊ ስራ በየመስኩ እየሰራች ትገኛለች፡፡በዚህም መንግስት ለወጣቱ በወጣቶች ፈንድ አማካኝነት ሰፊ የስራ እድል እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በሀገር ላይ ሰርቶ አግኝቶ ሕይወትን ለውጦ ለራስም ለቤተሰብም ተርፎ መኖር የሚቻልባቸው ሰፊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ይህንን መጠቀም እድሉን በማስፋት የራስን ስራ ማጎልበት ተወዳዳሪና ተፎካካሪ ሆኖ መውጣት ከወጣቱ በስፋት ይጠበቃል፡፡በዚህ መልኩ ስደትን እንዲሁም የሕገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎችን ድብቅ ሴራ መበጣጠስ ይቻላል፡፡

ከስደት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱት ስብእናን የሚነኩ ክብርን የሚያዋርዱ ድርጊቶች ብዙ ናቸው፡፡ ዜጎቻችን ይደፈራሉ፡፡ይገደላሉ፡፡ከፎቅ ይወረወራሉ፡፡ በአይኤስኤይኤስ እንደታረዱት ሁሉ በሌሎችም ቦታዎች ተመሳሳይ ድርጊት ሊገጥማቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ለወሲብ ንግድ ተገደው በሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ይሸጣሉ፡፡ክብራቸው ተገፎ ሰውነታቸው ተረስቶ ከአቅም በላይ እንዲሰሩም ይገደዳሉ፡፡እነዚህን የሚያጠናክሩ የሚገልጹ በርካታ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ፡፡

ስደትን ተከትሎ የሚመጣውን ብሔራዊ ክብርን የሚያዋርድ ድርጊት ለመግታት የረዥም ጊዜ ስራ ይጠይቀናል፡፡ልንሰራውም ግድ ይላል፡፡ከቀበሌ ጀምሮ በየደረጃው ባሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች መጠነ ሰፊ ስራ መሰራት አለበት፡፡ታች የሚሰራው ስራ ሰፊ ውጤቶችን ሊያስጨብጥ ይችላል፡፡

በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪነት የተሰማሩት ሰዎች ኑሮአቸውና ገበያቸው ስለሆነ ከዚህ ድርጊት ይታቀባሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው የሚሆነው፡፡ሕዝቡ ውስጥ ሰፊ ስራ ከተሰራ ግንዛቤው ካደገ ልጆቹ ወደ ስደት እንዳይወጡ ገንዘብም ስለሚከለክል የገቢ ምንጫቸውን ማድረቅ ማምከን ይቻላል፡፡በቅርቡ ሳኡዲ አረቢያ በሀገርዋ በሕገወጥ መንገድ ገብተው የሚኖሩና የሚሰሩ የውጭ ዜጎች ከምሕረት ጋር በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ እንዲወጡ አዋጅ አውጃለች፡፡

የእኛ ዜጎች በሳኡዲ በብዛት እንደሚኖሩ የታወቀ ቢሆንም እስካሁን ወደሀገራቸው ለመመለስ የተመዘገቡት ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡በሰው ሀገር ውስጥ ያለሕጋዊ ፈቃድ መኖር ለሚከተለው አደጋ ዋስትና የለውም፡፡የተሰጠው ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሳኡዲ መንግስት የሀገሩን ሕግ ለማስከበር በሚወስደው እርምጃ ችግሮች አደጋዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ከዚህ ሁሉ የሚመከረው ዜጎቻችን ወደ ሀገራቸው በሰላም እንዲመለሱ በሀገራቸውም ሰርተው መኖር የሚችሉበት ሰፊ እድል ያላቸው መሆኑን አምነው መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡

የሰው ወርቅ አያደምቅ እንዲሉ የሰው ሀገርም የሰው ነው የራስ መሆን አይችልም፡፡በግድ ከሕግ ውጭ ልኑር ማለትም አይቻልም፡፡ሳኡዲ አረቢያ በ1930ዎቹ ከአለማችን ድሃ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ነበረች፡፡የሀገሪቱን ሕይወት የለወጠው የነዳጅ ዘይት ሀብት መገኘት ነው፡፡ከዚያ በኋላ  ከተለያዩ የአለም ሀገራት ሰዎች እየተሰደዱ ወደ ሳኡዲ አረቢያ መጉረፍ ጀመሩ፡፡ብዙ የተማረ የሰው ኃይል ስለሌላት አብዛኛው ስራዎች የሚሸፈኑት ከፍተኛ እውቀትና ሙያ ባላቸው የውጭ ዜጎች ነው፡፡የቤት ሰራተኛነቱን ደግሞ በአብዛኛው ከአፍሪካ ሀገራት የሄዱ ስደተኞች ይሸፍናሉ፡፡

ኢትዮጵያ አሁን በያዘችው የኢኮኖሚ ልማትና እድገት በመቀጠል በብዙ መስክ የላቀ ደረጃ ላይ እንደምትደርስ ይታወቃል፡፡ለዜጎች ሰፊ የስራ መስኮች በየጊዜው እየተከፈቱ

ይገኛሉ፡፡ከድህነት መውጪያው ጊዜ ሩቅ አይደለም፡፡ይህ ሊሳካ የሚችለው እያንዳንዱ ዜጋ ሀገሬ ብሎ ለሀገሩ የተሻለውን ሁሉ በማድረግ በልማቱ ሲሳተፍ ስደትን ተጠይፎ በሀገሩ ላይ ጠንክሮ መስራት ሲችል ብቻ ነው፡፡በሰው ንግድ የተሰማሩ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን ከቀበሌ ጀምሮ በየደረጃው በማጋለጥ ለሕግ የማቅረቡ ስራ በራሱ በሕዝቡ በሰፊው ሲደገፍ የዜጎች ስደት አላስፈላጊ ሞት ውርደትና መከራም አብሮ ይወገዳል፡፡